# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ውሳኔዎች

የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩን አንድነትና ኅልውና ጠብቆ፥ ከአምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት ተላቆ፥ እኩልነትንና ፍትኅን አስፍኖ በደስታና በሰላም ለመኖር ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ለረዥም ጊዜ ታግሏል። በግንቦት ዘጠና-ሰባት ዓ.ም. ምርጫ ሚሊዮኖች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች የሄዱትና ድምፃቸውን የሰጡት የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ነው። ይኸ የሕዝባችን ቁርጠኛ አቋም በአሸባሪ አምባገኑ የሕወሐት/ ኢሕአዴግ የማን አለብኝና የግፈኛ አገዛዘ ተጨናግፎ፥ ሕዝባችን የጨለማ፥ የስቃይና የችግር ኑሮ እንዲገፋ ተገድዷል። ጨቋኝና አፋኝ የሆኑት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በርካታ ወገኖቻችንን በአደባባይ በመረሸን፥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ወደ ማጎሪያ ጣቢያዎች በመወርወር፥ በሺዎች ላይ ሰቆቃዊ ድርጊት በመፈጸም፥ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማኅበራትን በማፍረስና መሪዎቻቸውንና አባሎቻቸውን አስረው በማሰቃየት የሕዝባችንን ትግል ለማፈን ሞክረዋል። በዚህ ፀረ-ሕዝብ ድርጊታቸውም የለየላቸው አሸባሪ አምባገነኖች መሆናቸውን በግልጽ አረጋግጠዋል።

ከምርጫው ወዲህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይና መከራ በብዙ እጥፍ ተበራክቶና ተስፋፍቶ ሕዝባችን ሰብዓዊ ክብሩን ጠብቆ መኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከምርጫው በፊት በከባድ ትግልና በከፍተኛ መስዋዕትነት ተገኝተው የነበሩት የዴሞክራሲ ጭላንጭል መብቶች ሙሉ በሙሉ ተዘግተው ዛሬ መብትን ለመጠየቅም ሆነ ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ወይም በነፃ ሀሳብን ለማስፋፋት የማይቻልበት ብቻ ሳይሆን የማይሞከርበት አጠቃላይ የአፈና ሁኔታ ተፈጥሯል።

በአገዛዙ የተያዘው የለየለት ቅልበሳ እንደ መሆኑ መጠን የአገራችን ዴሞክራቶች ይኽንን የጥፋት ሂደት በጋራ ትግል ተረባርበው እስካላቆሙት ድረስ ይኸ የአፈና ውርጂብኝ በሽብር በተዋከበና በአመራር ክፍተት ግራ በተጋባ ኅብረተሰብ ውስጥ እንደሚቀጥል አጠያያቂ አይደለም። በአማራጭ ፕሮግራማችን ያጋለጥናቸው አጥፊ የአኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ቀጥለው በርሃብ፥ በአጣ በነጣ መናጢ ድህነት፥ በጂምላ ሥራ-አጥነት፥ በአካባቢ ውድመት ሆነ በሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች አገራችን የማትወጣው የቀውሶች አዙሪት ውስጥ እንደምትገባም መጠራጠር አይቻልም።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባገነን አገዛዝ ሽብርተኛነትን በመዋጋት ስም የባዕድ አገሮችን ተልእኮ ለማሟላት በሶማሊያ ላይ የፈጸመው ጣልቃ-ገብነትና እንዲሁም በአገሪቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች ሽብርተኛነትን በመዋጋት ሰበብ የውጭ ዜጎች የሚታሠሩበትና ሰቆቃዊ ድርጊት የሚፈጸምባቸው እስር ቤቶች ማቋቋሙ ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለተከታታይ ትውልዶች የሚተላለፍ ጠንቅ እየጋበዘ መሆኑ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ገሃድ የወጣ እውነታ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ የሰማሊያን የሽግግር መንግሥት ለመርዳት በሚል ምክንያት ወታደሮችን ወደ ሶማሊያ በመላክ ከእስላማውያኑ ኃይሎች ጋር ያደረገው ጦርነት የሕዝባችንን ደኅንነት ወይም አገርን

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ከውጭ ጠላት ለመከላከል የተደረገ እርምጃ ሳይሆን የውጭ ኃይሎችን ፍላጎት ለማሟላትና የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም የሚያስችል ድጋፍና ርዳታ በማግኘት አፈናውን ለማባባስ የተወሰደ ደንባራ እርምጃ ነው። አገራችን የውጭ ኃይሎች መናኸሪያና የሽብርተኞች መፈለያ ልትሆን መቻሏ የብዙዎች ስጋት ሲሆን ይኸም ሁኔታ የሕዝባችንን ደኅንነትና አንድነት እንዲሁም የአገራችን ክብርና ኅልውና አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ግልጽ ነው።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ከመጋቢት ፳፰ ቀን እስከ ሚያዚያ ፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. (April 6-9, 2007) በአሜሪካን አገር ሜሪላንድ ውስጥ ተካሄዷል። ለአራት ቀናት ያህል ሲካሄድ የቆየው ይኸ የብሔራዊ ሸንጎ አስቸኳይ ጉባዔ ከሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ፥ ከቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችና ከተግባር ኮሚቴዎች የቀረቡ ልዩ ልዩ ዘገባዎችን አዳምጦና ኅብረቱ ባለፈው አንድ ዓመት ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች በሰፊው መርምሮ፥ አገራችን ያለችበትን ሁኔታ በጥሞናና በጥልቀት በመገምገም የሚከተሉትን ግንዛቤዎች ወስዷል፤ ውሳኔዎችንም አሳልፏል።

1. ኅብረቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫነውን የግፍ አገዛዝ ለአንዴም ለሁሌም ለማስቆምና ይኸ አገዛዝ ተወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን ለማስቻል ሕዝባዊ ትግሉን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቦ ሁኔታውን የሚመጥን የተጠናከረ ሕዝባዊ ትግል እንዲካሄድ ወስኗል።

2. ትግሉን አጠናክሮ ወደ ሚፈለገው ግብ ለማድረስ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተለየ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመረዳት የኅብረቱ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ አስቸኳይ ጉባዔ በኅብረቱ ውስጣዊ ይዘት፥ አሠራሩና መመሪያዎች ላይ ጥልቅ ውይይት ካካሄደ በኋላ ትግሉን በተገቢው መንገድ ለመምራት የሚያስችል አሠራር፥ አመራርና አወቃቀር የሚያጠናና የመፍትኄ ሃሳብ የሚያቀርብ አንድ ኮሚሽን አቋቁሟል።

3. በእንጭጩ የተቀጨው የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) የግንቦት ድሎች የሚሊዮኖች የትግል ውጤት እንደነበሩ ሁሉ ከአሸባሪው አምባገነን አገዛዝ መልሶ ለመንጠቅ የሚቻለው በሚልዮኖች ዘርፈ ብዙ ተጋድሎ መሆኑን ኅብረቱ አምኖበታል። ይኸ ታግሎ የማታገል አደራ የሚሳካው በተናጠል ወይም በግል በሚደረግ ጥረት ሳይሆን በተባበረ ትግል ብቻ መሆኑን ኅብረቱ ካመነበት ውሎ አድሯል። ከዚህ በመነሳት ቀደም ብሎ ኅብረቱ ይኸን አስመልክቶ ያስተላለፈውን ጥሪ በማደስ ሦስተኛው አስቸኳይ የኅብረቱ የሸንጎ ጉባዔ ከኅብረቱ ጋራ በጋራ ትግል ጎዳና እንዲሰማሩ ለሁሉም ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎች በድጋሚ ጥሪ ያስተላለፈ ሲሆን ቀዳሚነትን በመውሰድ ፈቃደኛ የሆኑ ወገኖች ሁሉ በአስቸኳይ ተሰባስበው ጉባዔ የሚያካሂዱበትን ሁኔታ የሚያመቻችና በአስቸኳይ ተግባራዊ የሚያደርግ አንድ ግብረ-ኃይል አቋቁሟል።

4. የሶማሊያ ችግር መፍትኄ ሊያገኝ የሚችለው በሱማሊያ ሕዝብ የተባበረ ጥረት ብቻ መሆኑ እየታወቀ የተለያዩ ኃይሎችና አገሮች የየራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላትና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሱማሊያ ውስጥ ያደረጉትን ጣልቃ ገብነት ኅብረቱ ይቃወማል። ይኸ ጣልቃ ገብነት የብዙ ንጹህ የሶማሌ ዜጎችንና ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችንን ሕይወት በከንቱ እንዲቀጠፍ ያደረገ ከመሆኑ ሌላ በኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንና በሶሚሌ ዜጎች መካከል ያለውን የወንድማማችነት ስሜት የሚያበላሽ፥ በጎረቤት አገሮችና በኢትዮጵያ፥ በእስላምና በአረብ አገሮችና በኢትዮጵያ መካከል ሊኖር የሚገባውን መልካም ግንኙነት ያደፈረሰ፥ ሽብርተኛነት በአገራችን ይበልጥ ሊስፋፋ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቸ፥ ወደፊት በአገራችን ላይ ሆነ በሕዝባችን ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ ያላጤነ እርምጃ በመሆኑ ኅብረቱ እርምጃውን ኮንኖ በሁሉም

ባዕዳን ኃይሎች ዘንድ በሶማሊያ የተደረገው ጣልቃ ገብነት ባስቸኳይ እንዲቆም፥ መደበኛ ወታደሮችም ሆኑ ከሰብዓዊ እርዳታ ሰጭ ወገኖች ውጭ ያሉ ማናቸውም ጣልቃ-ገብ ክፍሎች በአስቸኳይ ወደየመጡበትና ወደየአገራቸው እንዲመለሱ በድጋሚ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ የአልቃይዳ መሪዎችና ሌሎች አክራሪ "እስላማውያን" ኃይሎች በአምባገነኑ አገዛዝ በሕወሓት/ኢሕአዴግ የተደረገውን ጣልቃ ገብነት በሕዝባችን ፈቃድ የተወሰደ እርምጃ አድርገው በመቁጠር በአገራችንና በሕዝባችን ላይ ያወጁትን የጂሃድ ጦርነት ኅብረቱ አጥብቆ ይቃወማል ፥ያወግዛል፡፡

5. አሸባሪው አምባገነኑ የኢሕአዴግ አገዛዝ የሕዝብ መብት እንዲከበር በመታገላቸው ብቻ በእስር ቤት አጉሮ የሚያሰቃያቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት፥ የሲቪክ ማኅበራትና የነፃው ፕሬስ መሪዎችና አባላት፥ ሠራተኞች፥ ገበሬዎች፥ ሴቶች፥ ወጣቶች፥ አዛውንት ወዘተ... በሙሉ ባስቸኳይ እንዲፈቱ ኅብረቱ ይጠይቃል፡፡ የፈጠራ ክስ በመመሥረት ሙሉ በሙሉ በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር በሚገኙና በሱም ፈቃድ ብቻ በሚሠሩ ፍርድ ቤቶች አማካይነት ጉዳያቸውን ለማየትና ፍርድ ለመስጠት እየተደረገ ያለው ትርዒት በፍትኅ ላይ የሚፈጸም ፌዝና አጉል አስመሳይ የማደናገሪያ እርምጃ በመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ የፍትኅ መኖርንም ሆነ አገዛዙ ለሕግ ተገዥነት ያለውን አቋም የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም ካለፈው ምርጫ ጋር በተያያዘ በግፍ የታሠሩትም ሆነ ላለፉት ዓመታት በየእስር ቤቱ ተወርውረው እየተሰቃዩ የሚገኙትና ደብዛቸው የጠፉ የፖለቲካና ኅሊና እስረኞች በሙሉ ባስቸኳይ እንዲፈቱ ኅብረቱ ይታገላል፡፡

<u>ጥሪዎች፤</u>

1. አምባገነኖችን በመፋለም ሕዝባችን ብዙ መስዋዕትነት የከፈለበትን ትግል በሁሉም መስክ አጠናክሮ እንዲቀጥል ኅብረቱ ጥሪ እያደረገ ትግሉን ዳር ለማድረስ የሚጠበቅበትን የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ከዚህ በፊት የገባውን ቃል ኪዳን በድጋሚ ያድሳል፡፡

2. ከሕዝብ የተነጠለውና በሕዝብ የተጠላው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባገን አገዛዝ የሕዝብን ግፊት በጥሬ ጉልበት ሁለንተናዊ አፈና በማስፈን በግፍ አገዛዝ ዕድሜውን ለጊዜው ማራዘም የቻለበት ዋናው ምክንያት ተቃዋሚ ኃይሎች ኃይላቸውን አስተባብረው የሕዝቡን ትግል በትክክል ሊመሩ አለመቻላቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የሕዝብን መብት ለማስከበርም ሆነ የአገሪቷን ሉአላዊነትና አንድነት ለማስጠበቅ ሙሉ እምነት ያላቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች ለሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ በተግባር ለሚገለጽ የጋራ ትግል በቁርጠኝነት እንዲነሱ ኅብረቱ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ኅብረቱ በዚህ ረገድ ሕዝባዊና አገራዊ ጉዳዮችን ዓላማ ላደረገ ማናቸውም የጋራ እንቅስቃሴ ያለውን ቁርጠኝነትና ሙሉ ዝግጁነቱን ይገልጻል፡፡

3. ዛሬ ዋናው የትግል አጀንዳ ኅብረተሰቡን ከዳር እስከዳር አስተባብሮና አንቀሳቅሶ የሕወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥት ከያዘው አደገኛ የጥፋት ሂደት ማስቆም እንደሆነ በጉባዔው ታምኗል፡፡ አሸባሪውን ሥርዓት በሕዝብ ትግል ከማንበርከክ በመለስ ምንም ዓይነት ዘላቂና አስተማማኝ መፍትኄ የለም፡፡ በአንዳንድ ባዕዳን ግፊትም ሆነ እግዛ ሕዝባችን በአመፅ የተነጠቁ ድሎቹን በድርድር ስም ከሕዝብ ጀርባ በሚካሄዱ መመሳጠሮች ለማምከን የሚደረገው አዘናጊ ሙከራም ይሁን "ያለፈው አልፏል ለሚቀጥለው ምርጫ ተዘጋጁ" በሚል አንዳንድ በተቃዋሚ ስም ያሉ ክፍሎችን ለማሳሳት የሚደረግ አነሁላይ ግርግር ወሳኙን የሕዝባችንን ትግል ግራ የሚያጋባ

አደገኛ አካሄድ በመሆኑ የአገራችን ዴሞክራቶች ድርጊቱን በአንድ ድምፅ አውግዘው ከዚህ ይልቅ በወሳኙ የሕዝባዊ ትግል ጎዳና እንዲሰማሩ ጥሪ እናቀርባለን።

4. ዛሬ ባለው የአገራችን ሁኔታ በምንም ምክንያት ይሁን በምን በዳተኛነት የምናባክናት እያንዳንዱዋ ሳምንትም ትሁን ወር የሕዝባችን የትግል ቅስም እየተሰበረ የሚሄድበትና ውሎ ሲያድር ትግሉ ከአሁኑ የባሰ የአቀበት ጉዞ የሚሆንበት አደጋ እንዳለ በመገንዘብ አገራችን የማትወጣው የቀውስ አዙሪት ውስጥ ከመግባቷ በፊት ወቅቱና ሁኔታው በሚጠይቁት ፍጥነትና ቆራጥነት ለሃቀኛና በተግባር ለሚገለጽ የጋራ ትግል እንድንነሳ ወገናዊ ጥሪአችንን እናቀርባለን።

5. ከግንቦቱ ምርጫ ወዲህ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የወሰዱትን የድምፅ ሰረቃና የሽብር እርምጃዎች በመቃወም አንዳንድ የምዕራብ አገሮች በአሸባሪው አገዛዝ ላይ የወሰዱት የማዕቀብ እርምጃ በውጭ እርዳታ እስትንፋስ አግኝቶ ይንቀሰቃስ የነበረውን አሸባሪ ቡድን ያስደነገጠ፥ ለሕዝባችን ተስፋ የሰጠ እርምጃ በመሆኑ በወቅቱ ኅብረቱ አድናቆቱን ገልጿል። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ የዓለም አቀፉን የሽብር ጦርነት ለመቋቋም ረዳት ይሆነናል በሚል አንዳንድ አገሮች በተለይም አሜሪካ ለአሸባሪው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የሚሰጡት የገንዘብ፥ የመሣሪያና የሞራል ድጋፍ አገዛዙ በሽብር ተግባሮቹ እንዲሰማራ ይበልጥ የሚያበረታቱት መሆናቸውን ኅብረቱ እየገለጸ፤ የሕዝብ መብት ገድቦ በአገሪቱ ዜጎች ላይ የሽብር ተግባሮችን የሚያካሂድ መንግሥት ዓለም-አቀፍ ሽብርን ለመቋቋም ይረዳናል ብሎ ማሰብ ትርጉም የለሽ ከመሆኑም በላይ የሽብር ተግባርን የሚያጠናክር፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለባሰ ስቃይና በደል የሚዳርግ እርምጃ መሆኑን ኅብረቱ በጥብቅ ያስገነዝባል። መንግሥታት ለአሸባሪው አገዛዝ እየሰጡ ያለውን ድጋፍና ትብብር እንዲያቋርጡ እየጠየቅን ሕዝባችን ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያደረገውን ትግል በመደገፍ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ እናደርጋለን።

በመጨረሻም በአገር ውስጥና በመላው ዓለም የተቋቋሙት የኅብረቱ የድጋፍ አካላት ኅብረቱ እያካሄደ ያለውን ትግል በመደገፍና ትግሉን ለማጠናከር ላበረከቱት ጉልህ አስተዋጽዖ ኅብረቱ ልባዊ አድናቆቱን ሲገልጽ ይበልጥ ውስብስና ጠመዝማዛ የሆነው ሕዝባዊ ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሁንም ድጋፋቸውና ሁለገብ ተሳትፏቸው እንዲቀጥል ኅብረቱ ጥሪውን ያስተላልፋል። ወደ ጉባዔው ተወካዮቻቸውን በመላክ ላደረጉትም አስተዋጽዖ ምስጋናውን ይገልጻል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ)

ሚያዚያ ፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.